# ከኢትዮጵያ ሕዝብ አርበኞች ግንባር የተሰጠ መግለጫ

አገራችን ኢትዮጵያ በጨካኙ ወያኔ እጅ ወድቃ በውስጧ የሚገኘው ሕዝባችን ከ 25 ዓመታት በላይ በሽፍታ አገዛዝ የመከራ ሕይወት በመግፋት ላይ ይገኛል። በአሁኑ ወቅት የሚታየው ሁኔታ እንደሚያመላክተው አጠቃላይ የአገሪቱና የሕዝቡ ሕልውና አደጋ ላይ ወድቋል። ፋሺስቱ ወያኔ የራሱን ክልል በማልማት ሌላውን በፈጠረው ዘረኝነት ምክንያት በገዛ አገሩ እየገደለና እየዘረፈ መሬቱን እየነጠቀ ስደተኛ አድርጎታል። ለምን ብሎ የሚጠይቀውንም ግዞት በማስገባት ያጉራል፤ ይገላል፤ ይሰውራል፤የህሊና ነፃነቱን ይገፋል። ይህ ዘራፊ ቡድን ዘላለማዊ ሆኖ ለመኖር እንዳሰበ የኢትዮጵያ ሕዝብ አርበኞች ግንባር በሚገባ ከተገነዘበው ውሎ አድሯል። ወያኔ ሓርነት ትግራይ በፀረ- ኢትዮጵያ አጀንዳ ተመስርቶ በአሁኑ ወቅት ኢትየጵያን የማፈራረስ ተግባሩን በማገባደድ ላይ ነው።

የኢትዮጵያ ህዝብ አርበኞች ግንባር ምርጫውን የትጥቅ ትግል አድርጎ ለረጅም አመታት ሲንቀሳቀስ መቆየቱን ማንም ያውቃል። በርካታ ፈተናዎችም አጋጥመውታል በአንድ በኩል የጠላት በሌላ በኩል በራሱ ውስጥ በሚፈጠሩ ችግሮች ተተብትቦ ትግሉን መራራ ቢያደርገውም ዋነኛው የህዝብ ጠላት የሆነውን ወያኔ በግንባር በመፋለም ከፍተኛ መስዋዕትነትን በመክፈል ላይ ይገኛል። ወያኔ በተፈጥሮው ሰላም፤ ልማት እድገት የአገርና የሕዝብ ደህንነት የሚባሉትን ፅንሰ-ሐሳቦችና የሕዝብ ምርጫዎችን አያውቃቸውም። ለወያኔ በቀላሉ የሚገባው በራሱ ተፈጥሮ የተካነበትን ግድያ ብቻ ነው። የኢትዮጵያ ሕዝብ አርበኞች ግንባር ገዳዩን ወያኔ ለማስወገድ የሚቻለው ከተቃዋሚዎች ጋር በህብረት ተጠናክሮ መስራት ሲቻል ነው ብሎ ያምናል። የተለያዩ የህብረትና የውህደት ጥሪዎችንም በማቅረብ ከበርካት ድርጁቶች ጋር ህብረት እየፈጠረ ለመስራት ሞክሯል። ግቦት 7 እያለ እራሱን ከሚጠራው ንቅናቄ ጋር የፈጠርነው ህብረትም ከላይ በጠቀስነው በጋራ አብሮ የመስራት ቅን ፍላጎት ላይ የተመሰረተ ግንኙነት ነበር። የኢትዮጵያ ሕዝብ አርበኞች ግንባር በጥር 2/2007 ከግንቦት 7 የፖለቲካ ድርጅት ጋር ውህደት ማድረጉም ወያኔን በጋራ ለመታገል በነበረው ፍላጎት ላይ ተመስርቶ ነው። "ጉድና ጅራት ወደሗላ እንደተባለው" ሆነና በአሁኑ ወቅት ግንቦት 7 ሌላ ጉድ ሆኖ አገኘነው።

በኢትዮጵያ ሕዝብ አርበኞች ግንባር አመለካከት ተባብሮ መስራት የተባለው ቅን ሐሳብ መሆኑ ቀርቶ ለጠላት ወያኔ የውስጥ ቡርቦራ ምቹ መንገድ የፈጠርንበት ሆኖ አግኝተነዋል። በመሆኑም የሚከተሉትን እውነታዎች ለኢትዮጵያ ሕዝብና ትግሉ ይመለከተናል ለሚሉ በተቃሞው ጎራ ለተሰለፉ ወገኖች እንዲሁም ለኢትዮጵያ ሕዝብ አርበኞች ግንባር በውጭም በውጥም ለሚገኙ አባላትና ደጋፊዎች መግለፅ ግድ ሆኖብናል። ጉዳዩን በዚህ ወቅት አደባባይ ማውጣት የፈለግነው በስሜት ተነሳስተን ወይም የግለሰብና የድርጅት ጥላቻ ኖሮብን ሳይሆን ይልቁንም መጀመሪያ ትግሉን ቀጥሎም ለትግሉ ውጤታማነት የከፈልነውን ክቡር መስዋዕትነት ገደል በማስገባት ለጠላት እጅ እድንሰጥ ወይም እንድንበተንና ሞታችንም ታሪክ የለሽ ለማድረግ የተነሳ የውስጥ ጠላት ስላጋጠመን ነው። ያሳየነው ትዕግስት ተሚጦ ያጋጠመን ፈተና ከባድ በመሆኑ እንድንዘረግፈው ተገደናል።

ውድ ኢትዮጵያዊያን

ግንቦት 7 እያለ እራሱን የሚጠራው ቡድን በአንድ ጎሳ ላይ ከፍተኛ ጥላቻ ያላቸው ጥቂት ግለሰቦች የመሰረቱት ንቅናቄ እደሆነ በውህደት ምስረታ ታሪካችን ውስጥ ተገንዝበናል። ከኛ ጋር ሕብረት ከመፍጠራቸው በፊት ከወያኔ ጋር በሁላ ደግሞ ቅንጅት ከተባለው ተቃዋሚ ድርጅት ጋር ይሰሩ እንደነበር ማንም የሚያውቀው ነው። ነገር ግን ወያኔን ያንቀጠቀጠው የቅንጅትና የሕዝባችን ሰላማዊ ትግል

የመጨረሻውን ውጤት እነዚሁ ግለሰቦች ከወያኔ ጋር ውስጥ ውስጡን በመዶለት ምን ያህል ጠልፈው እንደጣሉትና የህዝቡን መራራ መስዕዋትነት እንዴት መና እንዳስቀሩት  የትግል ስሜቱንና ሞራሉ እንዴት እደሰለቡት ለማንም የተሰወረ አልነበረም። ለበርካታ ወገኖቻችን መታሰር መገደል መሰደድ ምክያቱ ማን እደነበር ስናስታውሰ እጅግ ይሰማናል። ያሁሉ መስዋዕትነት ተከፍሎ የሕዝቡን ትግል  በመሸሽ ወደወጭ መጥተው መኖር ከጀመሩበት ጊዜ አንስተው አሁን እስካለንበት ድረስ  በውጭ የሚገኙትን ተቃዋሚ ድርችቶችና አገር ወዳዱን ዲያስፖራ ለማፍረስና ለማጭበርበር የተጓዙበትን እረጅም ጎዳና ስንመለከት ከወያኔ ተላላኪነት ውጭ ሌላ የሚመሳሰላቸው በጎ ነገር ባለማግኘታችን እጅግ ተገርመናል። ይሁንና ዲያስፖራውን በሚመለከት በኛ በኩል ለቀባሪ አረዱት ስለሚሆንብን ትዝብቱንና በታሪክ የሚኖረውን የተጠያቂነት ዕይታ ጉዳቱ ለደረሰበት ስደተኛው ሕዝባችንና በሰላማዊ መንገድ ለሚታገሉት የፖለቲካ ድርጅቶች ፍርድ ይሰጡበት ዘንድ መተውን መርጠናል።

እኛ በውስጥም በውጭም የምንገኝ የኢትዮጵያ ሕዝብ አርበኞች ግንባር  አባላትና ደጋፊዎች ምርጫችን የትጥቅ ትግል መሆኑን ወስነን ከጠላት ወያኔ ጋር ግብግብ በመግጠም ከፍተኛ መሰዋዕትነትን ስንከፍል መቆየታችን እንኳን ወዳጅ ጠላትም ይመሰክራል። ግንቦት 7  እውነተኛ ታጋይ ለመምሰል ያደረጉት ጮሌነት የተላበሰ ወያኔዊ ጭንብል እንኳንስ እኛን ቀርቶ ቀለሙንና ፖለቲካውንም ሆነ ወታደራዊ ሳይንሱን የገፉትን አዋቂዎች አሳስቶ ኢትዮጵያውያን ለአዳራሽ ጭብጨባና ዶላር ለማስታቀፍ ያነሳሳና ያደረሰ ስለሆነ እኛም የእነዚህን የውጭና የውስጥ ጠላቶች ተቀጣሪ የሆኑ ግለሰቦች የመሰረቱተን ግንቦት 7 የተባለ የንግድ ኩባንያ በወቅቱ ጉዳዩን አለማወቃችን (አለመንቃታችን) ሊፈረድብን እንደማይገባ እንናምናለን።

ስለሆነም የትጥቅ ትግል አራማጅ መስለው ህብረት እንድንፈጥርና የትጥቅ ትግሉን በጋራ እድናፋጥን ተደጋጋሚ ጥያቄ ሲያቀርቡ በውጭ በሚገኙ አንዳንድ ደገፊዎቻችን ጭምር በስራ አመራሩ ላይ ባደረጉት ግፊት ተገፋፍተን በጋራ ለመስራት ወሰን። አብዛኛው የግንባሩ አባላትና ደጋፊወች የነበራቸውን ጥርጣሬ ቢገለፁም በተግባር ማየቱ የተሻለ ነው በማለት ተቀባይነት ሳያገኙ ቀርተዋል። እራሳቸውን አግልለው ተመልካች ሆነው ነበር። በጋራ ለመስራት ስንወስን ግንቦት 7 የተባለው ንቅናቄ ፈርሶ ከአርበኞች ግንባር ጋር ለመጠቃለል በተስማማንበት ስያሜ ልንሰራ እንጅ በሺምቅ ተቀምጦ ሌላ ግዳጅ ተቀብሎ ሲፈልግ ከወያኔ ጋር ሲፈልግ ከምዕራባዊያንና ከአረቦቹ ጋር እየዋሸ የሌለውን አቅምና ተክለ-ሰውነት ፈጥሮ እኛ በማናውቀው ሁኔታ ከወያኔ ጋር ስልጣን ለመካፈል ተላላኪ ዲፕሎማት ይሆንብናልና፤ ይክደናል፤ ይሸጠናል፤ ይለውጠናል ብለን አንዳንችም  ጥርጣሬ አልነበረንም። በውጭ የሚገኘው ወገናችን ለትጥቅ ትግሉ መጠናከር ከፍተኛ ፍላጎትና የደጋፊነት ሚና ያለውን ሐይል በኛ ስም በማታለል መድረክ እያዘጋጀ ከፍተኛ ገንዘብ  ሰብስቧል። መስመር ላይ የሚገኘው ታጋይ ምንም ጠብ የሚል ነገር ሳይደረሰው ቀድሞ ባለበት ሁኔታ ላይ ይገኛል። እኛ በማናውቀው መንገድና ተጠያቂነት በሌለው ሁኔታ የተወሰኑ ግለሰቦች ደመወዝና የሆቴል፤የውሎ አበል ሆኖ መዝናኛ መጠጫና እንዲያ ሲልም ከመካከሉ ጎርበጥ ያሉ ከተገኙም የአፍ ማበሻ ይሆናል ብለን አልገመትንም። በትጥቅ ትግልም ይሁን በሰላማዊ የወያኔን አረመኔ ሽፍታ ቡድን በውጭ አገር ሆነው የሚቃወሙትን ተቃዋሚዎች እኛን በመሳሪያነት በመጠቀም በሚችሉት አቅም ሁሉ ወያኔን መቃወም እንዳይችሉ ማስፈራራት፤ ማሸማቀቅና ማዋከብ ይፈፀምባቸዋል ብለን አላሰብንም። በመካከላቸው መግባባትና መተማመን እንዳይኖር ከኔ በስተቀር ሌላ ተቃዋሚ በዲያስፖራው ውስተ እንዳይንቀሳቀስ ተብሎ ይታወጅባቸዋል ብለን አልገመትንም።

የተወደዳችሁ ኢትዮጵያዊያን !!

ግንቦት 7 ዕያለ ራሱን የሚጠራው ቡድን እንደተኮነነች ነፍስ የማይንጠለጠልበት ጉዳይ እንደሌለ ተግባሩ ምስክር ነው። ወያኔን የተቃወመና ውጤት ያስመዘገበ ተቃዋሚ ባለበት ቦታ ሁሉ እኔም አለሁበት ማለትና ሕዝብን ማሳሳት የግንቦ 7 ንቅናቄ ዋንኛ ተግባሩ ነው። ፖለቲካዊ መርሆዎቹና ፖሊሲዎቹ  መጨበጫ የሌላቸው የውሸት ንቅናቄ በመሆኑ እውነተኛ ገፅታውና ማንነቱን በሰሞኑ ከሌላ ድርጅት ጋር ባደረገው ስምምነት ለመረዳት አስችሎናል። የሚገርመው ደግሞ  ግንቦት 7 የውሸት ንቅናቄ ነው ብለው የሚቃወሙትን ወይም አስተያየት የሚሰጡ ግለሰቦችንና አገር ወዳድ ድርጅቶችንና መሪዎችን ሳይቀር በስድብ  የሚያሸማቅቁ ተሳዳቢዎችን መቅጠሩ ነው።

ከሁሉም በላይ የግንባራችን ወታደራዊ መምሪያ ሳያውቀው ተገቢነት ያላቸው የዘመቻ እቅድና አፈፃፀም ሳይወጣላቸው ዘመቻውም ተግባራዊ ሳይሆን ተዋጊ ሰራዊት ሳይዘምት ድል ተጎናፅፈናል ይህን መሬት ተቆጣጥረናል ይህን ያህል ገለናል በማለት ከየት ሆኖ የሚወጣ መግለጫ እንደሆነ በማናውቀው መንገድ የተነፋው ፊሺካ የሚነፋው ጡሩንባ እጅግ አሳዛኝ ሆኖ  አግኝተነዋል። የዘመቻውን የድል ዜናና ሐላፊነት የመውሰዱን ጉዳይ ጠለቅ ብለን ማጥናትና ማወቅ ስለነበረብን መደምደሚያ ሆኖ ያገኘነው ለጠላት ወያኔ በሚጠቅም መንገድ የመረጃ ስራ እየተሰራበት መሆኑን ለማረጋገጥ በቅተናል። ሰው በላው ወያኔ ከኛ ጋር ምንም አይነት ግንኙነት የሌላቸውን ወገኖች ግንኙነት እንዳላቸው በማስመሰል እንዲያውም አሸባሪዎች ናቸው በሚል ምክንያቱ ሲቪል ወገኖቻችን እያረደና በየ እስር ቤቱ እያጎረ ሐብት ንብረታቸውን እየዘረፈ የግፍ ዶፍ ሲያወርድባቸው አስተውለናል። ይህ ለወያኔ እንዲጠቅም ተደርጎ የተቀመረው የግንቦተ 7 የውሸት ወታደራዊ መግለጫ ውጤት ነው። በዚህ አጋጣሚ በኛ ስም በውሸት በሚለቀቅ  የወታደራዊ ድል መግለጫ ምክንያት ከፍተኛ ጉዳት ለደረሰባቸው ወገኖቻችን ታላቅ ሐዘናችን እየገለፅን ሐላፊነቱን የሚወስደው ግንቦት 7 እያለ እራሱን የሚጠራው እና ወያኔዎች መሆናቸውን በታላቅ ይቅርታ በአክብሮት እናሳስባለን። ግንቦት 7 እንኳንስ ወታድራዊ ድል የሚያጎናፅፍ ወታደር ሊኖረው ቀርቶ የጦርነት ቀጠናውን የጎበኘ አንድ ወታደር እንደሌለው ስንገልፅ  በእርግጠኝነትም ነው።

በመጨረሻም በመላው ዓለም ለምትኖሩ ኢትዮጵያውያንና ለረጅም ጊዜ ወያኔ የተባለውን ጠላት በመታገል ላይ ለሚገኙት ተቃዋሚ ሐይሎችና ታላላቅ ምሁራን !!

**የኢትዮጵያ ህዝብ አርበኞች ግንባር በሺ የሚቆጠሩ አባሎቻችንና ደጋፊዎቻችን የተሰውብን ግንባር ነው። የተረፍነውም ሰውበላውን የወያኔ ስራዓት ለማስወገድ አሁንም በዱር በገደል እየተፋለምን የምንገኝ በመሆናችን ግንቦት 7 የተባለውን ንቅናቄ እመራዋለሁ ለሚሉት ዶክተር ብርሀኑ ነጋ የሚከተሉትን ጉዳዮች ማስተላለፍ እንወዳለን። እስካሁን የፈፀማችሁት ማታለልና ማጭበርበር ከዚህ ላይ በቂ ሆኖ መቆም አለበት ። ሕዝባችን እያደረገ ያለወ መራራ ትግል (ሕዝባዊ እምቢተኝነት) ውጤት ያለውና ስኬታማ እንዲሆን ከተፈለገ እንዲሕ ያለው ማጭብርበርና የቅጥፈት ፖለቲካ ወያኔ የተጓዘበት መንገድ ስለሆነ መደገም ስሌለበት ለአንዴና ለመጨረሻ ጊዜ መቆም እንዳለበት የኢትዮጲያ ሕዝብ አርበኞ ግንባር ያምናል።**

**ግንቦት 7 የተባለው ንቅናቄ ከኛ ከኢትዮጵያ ሕዝብ አርበኞች ግንባር ጋር ያለውን ውሕደት ያፈረሱት እርሰዎ ዶክተር ብርሐኑ  ስለሆኑ እኛም እርሰዎንና እመራዋለሁ የሚሉትን ንቅናቄ በሚገባ መርምረንና ጥናት አካሔደን መረጃዎችን አሰባስበን የሚጓዙበት የፖለቲካ አካሔድ ሕዝባችን ውድቀት ላይ የሚጥለው መሆኑን ተገንዝበን የኢትዮጵያ ሕዝብ አርበኞች ግንባር እራሱን ችሎ መንቀሳቀስ እንዳለበት በማመን ከፈጠርነው ውሕደት ያሰናበትነዎት ስለሆነ ይህንኑ ግንዛቤ በማስገባት በስማችን የሚያደርጉት ማንኛውም ፕሮፓጋንዳ ተቀባይነት የለውምና እንዲያቆሙ እንጠይቃለን።**

- ንቅናቄዎት ለድርጅታችን ማጅራት መች ከኋላ በማስቀመጥ ሰራዊታችን ለማዳከምና ጨርሶ ለማጥፋት የተጓዘበትን እረጅም መንገድ ደርሰንበታል። ታጋይ መስላችሁ በመቅረብ ያደረሳችሁብንን የህይወት፤የንብረትና የሞራል ኪሳራ ቀላል ባለመሆኑ በተጠያቂነት እንደምንፈልገወት መላው የኢትዮጵያ ሕዝባችንና መላው ተቃዋሚ ድርጅቶች አገር ወዳድ ምሁራን እንዲያውቁት ስንጠይቅ በየትኛውም ቦታ የሚገኙ የግንባሩ አባላትና ደጋፊዎች በያሉበት ሆነው ጉዳዩን በንቃት እንዲከታተሉ እናሳስባለን፤
- ግንቦት 7 የተባለው ንቅናቄዎት አንድም የታጠቀ ወታደር አለመኖሩን እያወቁ ዛሬ በአገራችን ውስጥ ሕዝቡ መሮት ስላመፀ በወያኔ ላይ የሚወስዳቸውን እርምጃዎች ለማሰናከልና ለመቀማት ትጥቅ አስታጥቅው ቀለብ ሰፍረው የዘመቻ እቅድ አውጥተው ግዳጅ አሰማርተው ወታደራዊ ድል ያስመዘገቡ በማስመሰል የወረቀት እሩምታ ተኩስ እያሰሙ ያልዋሉበትን፤ የማያውቁትን የድል ነጋሪት እየጎሰሙ የውሸት ድል አድራጊትን እየሰበኩ ነው። ለጠላት ወያኔ መረጃ በመስጠት ቁጥሩን በትክክል መግለፅ ያልቻልነው ወገናችን ለጠላት ጥይት ድብደባና ለግዞት እንዳበቁት እርሰዎ እራሰዎ ያውቁታልና ለጠፋው የሰው ሕይወት፤ ለጠፋው ንብረት፤ በማጎሪያ ቤት ለሚሰቃየው ወገናችን ተጠያቂው የአርበኞች ግንባር ሳይሆን እርሰዎ ለመሆነወት አጠያያቂ አይሆንም።
- እንደሚያወቁት ንቅናቄዎት ግንበት 7 ግልፅ የሆነ የፖለቲካ አጀንዳና ኢትዮጲያዊ ስሜት የሌለው ለመሆኑ ባሳለፍናቸው ቆይታዎች በሚገባ አረጋግጠናል። ከኛ ከተሰናበታችሁ በኋላ ሰሞኑን ደግሞ

የሰላም ታጋዮች ሆናችሁ ከአቶ ሌንጮ ጋር በአርበኞቻችን ስም ድርድር ማድረጋችሁ እጅግ ያሳፍራል።

- የትጥቅ ትግሉ የበለጠ ይጠናከራል በሚል ቅን ፍላጎት ያለው ዲያስፖራው ወገናችን እኛን እየደወለ ከማበረታታ አልፎ ገንዘቡን በእርሰዎ አካውንት በማስገባት ለግሷል። ነገር ግን ተገኘ ከተባለው የድጋፍ ገንዘብ በግዳጅ ላይ የሚገኘው ሰራዊት የደረሰው ነገር የለም። ስለጉዳዩ ልናነጋግረወት ፈልገን የሚኖሩት ከኛ ከሰራዊቱ በብዙ ማይልስ እርቀው አውሮፓ ይሁን አሜሪካ የት እንደሚኖሩ ስላማናውቅ ሳይሳካልን ቀርቷል። በጋራ አመራር የማያምኑ አምባገነን ከመሆነወትም በላይ ከኛ የተሰወረ ድብቅ ኮሜቴ አቋቁመው የተገኘውን ገንዘብ ለናንተ ደመወዝና የሆቴል አልጋ፤የመዝናኛ የቀን አበል እንዳዋላችሁት በሚገባ እናውቃለን። ከዚህ ላይ ለማስገንዘብ የፈለግነው መጀመሪያም ወያኔን በትጥቅ ትግል ከስልጣኑ ለማባረር አምናችሁበት ሳይሆን እኛን በማፍረስና በማጥፋት ላይ የተመሰረተ ቢዝነስ ከወያኔ ጋር እርሰዎ እንደመከሩብን እኛም አውቀንበወታል። ስለዚህ እናንተም በኛ ደም ቀልዳችሁ የተመኛችሁትን ስልጣን ከወያኔ ጋር ተካፍላችሁ በተራችሁ የጎሳ ፌደራል ስርዐት ወንበር ተቀብላችሁ ኢትየጵያን ለመግዛት ያብቃችሁ እኛም ከታላቁ ሕዝባችን ጋር ሆነን እርሰዎና ወያኔ በደገሳችሁልን ጥፋት ስታጠፉን እናያለን____.////-----

ለሁሉም ጊዜ አለው !!

የኢትዮጵያ ሕዝብ አርበኞች ግንባር !!